የጻድቃን ትንሣኤ

ከተስፋዬ ሮበሌ

ይህ ወንድም ተስፋዬ ሮበሌ፣ *“በሥጋ ትንሣኤ አምናለሁ! የአስተምህሮተ ትንሣኤ መጽሐፍ ቅዱሳዊ፣ ታሪካዊና ሥነ አመክንዮአዊ ትንታኔ”* በሚል ርእስ ካዘጋጀው መጽሐፍ፣ ከምዕራፍ ዘጠኝ በቀጥታ የተወሰደ ነው። በሙታን ትንሣኤ ላይ ሰፊ ማብራሪያ ከፈለጉ ይህን መጽሐፍ እንዲያነቡ እናበረታታለን።

በቅዱሳት መጻሕፍት የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ከጻድቃን ትንሣኤ ጋር በብዙ መልኩ ተያይዞና ተነጻጽሮ ይገኛል

1. **ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን በቅርቡ ትቶአቸው እንደሚሄድ የተናገረው በቅርቡ ዳግም እንደሚያዩት ተስፋ በመስጠት ነው፤ ይህም እርሱ ሕያው እንደ ሆነ እነርሱም ሕያዋን እንደሚሆኑ ታሳቢ ያደረገ ንግግር ነው** (ዮሐንስ 14÷18-19 አመት)።

2. **ኢየሱስ በሞተበትና በአካለ ሥጋ ከሙታን ከተነሣበት ጊዜ መካል በኢየሩሳሌም የበርካታ ሰዎች መቃብር እንደ ተከፈተ ሙታንም እንደ ተነሡ ማቴዎስ ዘግቦልናል** (ማቴዎስ 27÷51-53 አመት)። **በርካታ ሊቃውንት ይህ ክሥተት ወደ ፊት በትንሣኤ ቀን የሚሆነውን ነባራዊ እውነታ የሚያሳይ ናሙና እንደ ሆነ ያስረዳሉ።**

3. **በትንሣኤ ሙታን የማያምኑት ሳዱቃውያን በመባል የሚታወቁት የአይሁድ የሃይማኖት ክፍሎች፣ ደቀ መዛሙርት የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሣኤ መዕከል ባደረገ መልኩ የሙታንን ትንሣኤ ማስተማራቸው እጅግ አሳስቦአቸው ነበር** (ሐዋርያት ሥራ 4÷1-2 አመት)። **ይህ ክፍል በሚገኝበት ዐውድ ውስጥ የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ** (ሐዋርያት ሥራ 3÷15:26 አመት) **ከጻድቃን ትንሣኤ ጋር ተቈራኝቶ ቀርቦአል** (ሐዋርያት ሥራ 4÷2 አመት)።

4. **ሐዋርያው ጳውሎ የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሣኤ በኩራት እያለ መጥራቱ፣ የጻድቃን ትንሣኤና የኢየሱስ ትንሣኤ ተመሳሳይ ገጽታ እንዳላቸው እንዲሁም ተከታትለው የሚሆኑ ክሥተቶች እንደ ሆኑ የሚያመለክት ነው** (ሐዋርያት ሥራ 26÷23 አመት)።

5. **የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሣኤ ከጻድቃን ትንሣኤ ጋር የሚያዛምደው ሌላው የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ** (2ቆሮንቶስ 4÷7-5÷10 አመት) **ነው። ጳውሎስ በዚህ ክፍል ላይ የሚናገረው ክርስቲያኖች ስላለባቸው ስደት፣ መከራ እንዲሁም ሞት ሲሆን፣ ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው አምላክ ክርስቲያኖችንም ከሙታን እንደሚያስነሣቸው ይገልጻል** (2ቆሮንቶስ 4÷14 አመት)። **ሐዋርያው ተደራስያኑ በዘላለም ሕይወት ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ በሚያስገነዝብበት ወቅት በሞትና በዘላለም ሕይወት መካከል ስለሚገኘው የሽግግር ወቅት ይናገራል** (2ቆሮንቶስ 5÷1-9 አመት) (intermediate state)። **ሐዋርያው በዚህ የሽግግር ወቅት ጻድቃን ቁሳዊ አካላቸው ትንሣኤ እስከሚያገኝ ድረስ ያለአካል** (disembodied state) **ይህ በሞትና በትንሣኤ መካከል ያለው ቆይታ የተባረከ ቆይታ እንደ ሆነ ይገልጻል፤ ቆይታው ቡሩክ ለመሆኑ ዐቢይ ምክንያት ተደርጎ የተጠቀሰው ያለአካል መሆናችን በጌታ ዘንድ መሆናን በማስቻሉ ነው** (2ቆሮንቶስ 5÷8 አመት)።

6. **በሞትና በትንሣኤ ጊዜ መካከል ስለሚገኘው የሽግግር ወቅት ከሚናገሩት የሐዲስ ኪዳን ምንባባት መካከል** (ፊልጵስዩስ 1÷21-23 አመት) **አንዱ ክፍል ነው::**

"በእነዚህ በሁለቱ እጨነቃለሁ፤ ልሄድ፣ ከክርስቶስም ጋር ልሆን እናፍቃለሁ፤ ይህ *እጅግ የተሻለ ነውና (ፖሎይ ማሎን ክሬይሶን)*" (ፊልጵስዩስ 1÷23 አመት)

ቀጥታር 21 **ላይ** "*ለእኔ፣ መኖር ክርስቶስ ነው፤ ሞትም ማትረፍ*":: "ትርፍ ነው/ጥቅም ነው (*ክርዶስ*)" **የሚለው ቃል እንዲሁም** "*እጅግ የተሻለ ነውና/ከሁሉ ይልቅ እጅግ የሚሻል ነውና (ፖሎይ ማሎን ክሬይሶን)*" **የሚለው ሐረግ ከክርስቶስ ጋር መሆን እጅግ ትልቅ ጠቀሜታ እንዳለው እንዲሁም አሁን በሥጋ የምንኖርበት ሕይወት ሊመጣ ካለው ሕይወት ጋር በጭራሽ ሊነጻጸር እንደማይችል የሚያስተምር ነው—መሞትና ከክርስቶስ ጋር ኑሮ መጀመር እጅግ ተመራጭ ጉዳይ ነው::**

7. **በሞትና በትንሣኤ መካከል ስለሚገኘው የሽግግር ወቅት የሚናገሩ በርካታ የሐዲስ ኪዳን ምንባባት አሉ:: ኢየሱስ አብሮ ስለተሰቀለውና እርሱን ለዘላለም ሕይወት ተስፋ ስላደረገው ወንበዴ የገለጸለት ጉዳይ ከሞቱባት ቅጽበት በኋላ ሕይወት እንደሚጀምር የሚያስተምር ነው::**

"ኢየሱስም፣ 'እውነት እልሃለሁ፤ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ' አለው" (ሉቃስ 23÷43 አመት)

በሞትና በትንሣኤ መካከል ስለሚገኘው የሽግግር ወቅት የሚናገሩ ተጨማሪ ሁለት የሐዲስ ኪዳን ክፍሎች ሉቃስ 16÷19-31 **እና ራእይ** 6÷9-11 **ናቸው:: ስሙ ስላልተጠቀሰው ባለጠጋው ሰውና ስለ ድኻው አልዓዛር የሚናገረው የሉቃስ** 16÷19-31 **ክፍል እነዚህ ሰዎች በሞቱበት ቅጽበት ሁለት ተቃራኒ ወደ ሆኑ ስፍራዎች እንደሚሄዱ የሚያመለክት ነው:: ጻድቃን በገነት ጎጥኣን ደግሞ በሲኦል ይቆያሉ:: ሲኦል፣ ጎጥኣን ከነጭ ዙፋን ፍርድ/ታላቁ የፍርድ ቀን የመጨረሻውን ፍርድ እስከሚያገኙ ደርስ የሚቆዩበት ስፍራ ሲሆን፣ ገነት ደግሞ ጻድቃን ወደ መንግሥተ ሰማይ ከመሄዳቸው በፊት የሚቆዩበት ስፍራ ነው:: ራእይ** 6÷9-11 **ባለው ክፍል በሞትና በትንሣኤ መካከል ስለሚገኙ የሰዎች ነፍሳት የሚያወራ ሲሆን፣ እነዚህ ነፍሶች በጌታ ዘንድ ንቁ ሆነው እንደሚኖሩ የሚያስተምር ነው::**

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ዘአፈጸመኒ በዳኅና